# ምድብ ሁለት (ከ1ኛ — 3ኛ) ክፍል

## 33 ኛ ሳምንት

## ምሕረት የተደረገለት ወንጀለኛ

### ዓላማ

❖ እኛ ምሕረት ከጠየቅነው እግዚአብሔር ይምረናል።

### ምንባብ

❖ ሉቃ 23

### መግቢያ

❖ የስቅለትን ታሪክ ታስታውሳላችሁ? የስቅለት ታሪክ ክርስቶስ በመስቀል ስለኛ የተቀበለው መከራ ታሪክ ነው።ይህን መከራ የተቀበለው ከዘላለማዊ ሞት ሊያድነን ነው።

❖ በዛሬው ትምህርታችንም ጌታ በመስቀል ላይ ምህረት ስላደረገለት ወንጀለኛ እንማራለን።

### ትምህርቱ

❖ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በተሠቀለ ጊዜ፣ ሌሎች ሁለት ሰዎችም ሞት ተፈርዶባቸው በመስቀል ላይ ተሰቅለው ነበር። አንደኛው በቀኝ ሌላውም በግራ ነበር የተሰቀሉት።

❖ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የሠቀሉት ከመስቀል ሥር ሆነው ***"የአይሁድ ንጉሥ ሆይ ራስህን አድን ..."*** ሲሉ ያጉረመርሙ ነበር። ጌታችን ግን አልመለሰላቸውም ነበር። እንዲያውም ***"አባት ሆይ የሚሰሩትን አያውቁምና ይቅር በላቸው"*** ሲል ጸለየላቸው።

❖ ከተሠቀሉት ወንጀለኞች በግራ የነበረው ***"አንተ ክርስቶስ ከሆንክ ራስህንም ሆነ እኛን አድነን"*** ይል ነበር።

❖ በቀኝ የተሰቀለው ወንጀለኛ ግን ***"አንተ እግዚአብሔርን አትፈራውምን? ... እኛ... ስላደረግነውም የሚገባንን እንቀበላለንና በእኛስ እውነተኛ ፍርድ ነው፤ ይህ ግን ምንም ክፋት አላደረገም ብሎ ገሠጸው።"***

❖ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በተሰቀለበት ጊዜ ብዙ ተዓምራት ተፈጸመዋል።ምድር ሲነዋወጥ፣ፀሐይ ጨልሚል፣ ከሙታንም ብዙ ተነሱ።

❖ በቀኝ የተሰቀለው ወንበዴም ይሄን ሁሉ አይቶ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን አመነ። በግራ የተሠቀለውን ከወቀሰ በኋላም ወደ ጌታ ዞሮ ***" ጌታ ሆይ፣ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ"*** አለ።

❖ ጌታችንም ***" ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ"*** አለው። ኢየሱስ ክርስቶስ እምነቱንና ንስሐውን ተቀበለለት።

❖ በመስቀል ሥር ለነበሩትና ለሚሰድቡት ያልመለሰውና የጸለየላቸው ክርስቶስ ምህረት ለጠየቀው ወንጀለኛ በገነት ከእርሱ ጋር እንደሚሆን መለሰለት። ወደ ገነት ለመግባትም የመጀመሪያው ሰው ሆነ።

### መዝሙር

ጥልን በመስቀሉ ገደለ (2)
በመስቀሉ ለሰው ልጅ ሠላምን አደለ (4)

**ይቆየን።**